# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
# የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የሰ.መ.ቁ 234680

ቀን ጥቅምት 6 2016ዓ.ም

**ዳኞች፡** እትመት አሰፋ

ደጀኔ አያንሳ

ብርቅነሽ እሱባለው

ሀብታሙ እርቅይሁን

ብርሃኑ መንግስቱ

**አመልካቾች፡** 1ኛ. ወ/ሮ መቅደስ ተስፋዬ

2ኛ. ወ/ት ራሄል ተስፋዬ

**ተጠሪዎች፡** 1ኛ. ወ/ሮ ለምለም ግርማ

2ኛ. ወ/ሮ ንግስቴ መኮንን

3ኛ. የሐረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት የግንባታ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ማሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

# ፍርድ

ጉዳዩ ለሰበር ችሎቱ የቀረበው አመልካቾች የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረሪ ሕዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20189 በ20/7/13ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ፤ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 05597 በ11/4/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00274 በ21/10/14ዓ.ም በሰጠው ውሳኔ ቅር በመሰኘት በ11/1/15ዓ.ም በተጻፈ የሰበር አቤቱታ ስላቀረቡ ነው፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አመልካቾች በስር የሐረሪ ሕዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ ባቀረቡት ክስ በሐረር ከተማ ሐኪም ወረዳ ቀበሌ 17 የቤ.ቁ 664 የሆነው በስማችን ተመዝግቦ የሚገኘው ይዞታ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ቀድሞ ያልነበረውን ከራሳቸው ግቢ የሚወጣ ጎርፍ ቀድሞ ይወጣበት የነበረውን የጎርፍ መሄጃቸውን በመቀልበስ የይዞታዬ አካል የሆነውን በስተደቡብ የድጋፍ ግንብ ከብር 80,000.00 በላይ አውጥቼ የገነባሁትን የድጋፍ ግንብ አደጋ ላይ በሚጥል መልኩ የአጥሩን ብሎኬት በመብሳት ፍሳሽ እየለቀቁበት ጉዳት እንዲደርስበት እያደረጉ ከመሆኑም በላይ ከህግ አግባብ ውጪ አመልካቾችን በሚጎዳ መልኩ ግቢ ውስጥ እንዲያልፍ በማድረግ ግንቡን ለመጠቀም እንዲችሉ 3ኛ ተጠሪ ፈቅዷል፡፡ 1ኛ ተጠሪ ሰርቪስ በገነቡበት ወቅት ከአመልካቾች የድጋፍ ግንብ 0.50ሜትር ርቃ እንድትሰራ በ3ኛ ተጠሪ ታዛ ሳትሰራ በመቅረቷ ይህ ጥፋት መሆኑን ጠቅሶ ባለስልጣኑ የራሱ ባለሙያዎች በሰጡት አስተያየት የቀድሞ ግንባታ እንዲፈርስ በተባለበት ሁኔታ በህገ ወጥ መንገድ በገነባችው ሰርቪስ ቤት ውስጥ ለውስጥ በቱቦ በማምጣት የድጋፍ ግንብ አጥሬ ላይ እያፈሰሰች ሆና ሳለ 3ኛ ተጠሪ ፍሳሽ ከግቢዋ እንዲወጣ መፍቀዱ አግባብ ባለመሆኑ 1ኛ ተጠሪ ከጅምሩ ቀድሞ የነበረን የድጋፍ ግንብ አጥሬ ላይ 0.50 ሜትር ገባ ብላ መገንባት ሲገባት ይህን ባለመፈጸም በይዞታዬ ውስጥ የሚያልፍ ጎርፍ ባልነበረበት አሁን የጎርፍ መውጫው በይዞታዬ እንደሆነ በማድረግ ከ2ኛ ተጠሪ የሚያዋስነን ግንብ ላይ ጉዳት ያደረሰ በመሆኑ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች እየፈጸሙ ያሉትን የሁከት ተግባር እንዲያቆሙ እንዲወሰን፤ 3ኛ ተጠሪ የጎርፍ አቅጣጫን ከግንዛቤ ሳያስገባ የ1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎችን ህገወጥነት አረጋግጦ ሳለ በይዞታየ ውስጥ ፍሳሽ ይለፍ ማለቱ አግባብ ባለመሆኑ የተሰጠው ትእዛዝ እንዲነሳ እንዲወሰንልኝ፤ 1ኛ ተጠሪ ከአጥር 0.50ሜትር ርቃ መገንባት ሲገባት አጥሬን አስደግፋ የሰራቸው ግንብ እንዲነሳ እንዲወሰንልኝ፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በግቢያቸው በኩል በግንባችን ላይ ያደረሱትን ጉዳት ፍ/ቤቱ በባለሙያ እንዲያስገምትልንና ለጉዳቱም ሀላፊ ናቸው በማለት የጉዳት መጠኑ ባልተነጣጠለ ሀላፊነት ተጠሪዎች እንዲከፍሉ እንዲወሰንባቸው በማለት ዳኝነት ጠይቀዋል፡፡ ማስጃዎችንም አቅርበዋል፡፡

ተጠሪዎች የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያዎችን እና በፍሬጉዳዩ ላይም መልስ በማቅረብ የተከራከሩ ሲሆን ፍ/ቤቱ መቃወሚያዎቹን በብይን አልፏቸዋል፡፡ ከዚሁ በኋላ ፍ/ቤቱ በፍሬጉዳዩ ላይ የአመልካቾችን እና

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

የተጠሪዎችን ምስክሮች በመስማት ከሰነድ ማስረጃዎች ጋር ጉዳዩን ጭብጦችን በመያዝ መርምሮ ተጠሪዎች በአመልካቾች ግቢ ውስጥ የውሃ ፍሳሽ እንዲፈስ በማድረግ የፈጸሙት ሁከት የለም በማለት ወስኗል፡፡ እንዲሁም አመልካቾች ተጠሪዎች ጉዳት አድርሰውብናል በማለት በጠየቁት ዳኝነት ላይ የቀረበ ማስረጃ ስለሌለ ፍ/ቤቱ አልተመለከተውም በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጸው ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኝ ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማጽናት ወስኗል፡፡ በዚሁ ላይ አመልካቾች የሰበር አቤቱታ ለሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት አቅርበው ፍ/ቤቱም የተጠሪዎችን መልስ ተቀብሎ ለክርክሩ መነሻ የሆነውን ጉዳይ በተመለከተ የሐረሪ ክልል የመሬት ልማት ማኔጅመንት ሙያተኛ መድቦ ስለጉዳዩ እንዲያሳውቅ በሰጠው ትእዛዝ መሰረት ምላሽ ከቀረበለት በኋላ ጉዳዩን መርምሮ የስር ፍ/ቤቶችን ውሳኔ በመሻር ተጠሪዎች ቁጥሩ እና ቀኑ በተገለጸ ከግንባታና ቁጥጥር ባለስልጣን በተሰጣቸው ፈቃድና ፕላን ተጠቅመው የሚቀበረው ቱቦ በደለል እንዳይሞላና መነሻው ላይ ውጫዊ ልኬቱ 1ሜትር በ1ሜትር የውስጥ ልኬቱ 0.6 ሜትር በ0.6 ሜትር የሆነና ጥልቀቱም ከ0.7ሜትር የሚያንስ ሆኖና በ1ኛ አመልካች ግቢ ውስጥ የሚቀበረው ቱቦ ግቢዋን በማያበላሽ መልኩ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በራሳቸው ወጪ እንዲያሰሩ በማለት ወስኗል፡፡

አመልካቾች ከላይ በተገለጹት ውሳኔዎች ቅር በመሰኘት ለዚህ የሰበር ሰሚ ችሎት ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ በስር ፍ/ቤቶቹ ውሳኔ ተፈጽመዋል የሚሉትን መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት በመዘርዘር እንዲሻር እና ተጠሪዎች በአመልካቾች ላይ የፈጠሩት ሁከት እንዲወገድ፤ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች ፍሳሻቸው በአመልካቾች ይዞታ ላይ እንዲያልፍ የተሰጠው ውሳኔ እንዲሻርልን፤ 1ኛ ተጠሪ የአመልካቾችን አጥር አስደግፋ የሰራቸው ግንብ እንዲፈርስ እንዲታዘዝልን፤ በአመልካቾች አጥር ላይ የደረሰው ጉዳት በባለሙያ ተገምቶ፤ ወጪና ኪሳራን ጨምሮ እንዲከፈለን እንዲወሰንልን በማለት ጠይቀዋል፡፡

የአመልካቾች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪ ችሎቱ ተመርምሮ ተጠሪ ለክርክር ምክንያት የሆነው የፍሳሽ መውረጃ ቱቦ በተመለከተ የግንባታና ቁጥጥር ባለስልጣን በፈቀደላቸው መሰረት ያልገነቡትና ተጠሪዎች ሊጠቀሙት የሚችሉት ሌላ አማራጭ ያላቸው መሆኑና አሁን የገነቡት የፍሳሽ መሄጃ ቱቦ በአመልካቾች አጥርና ግቢ ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑን ፕላን በማያያዝ ስር ፍ/ቤት ምላሽ የቀረበ መሆኑ በተገለጸበት ሁኔታ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት በአሁን ተጠሪ ግቢ በማያበላሽ መልኩ ቱቦ እንዲቀበር የወሰነበትን አግባብነት ለመመርመር ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ይቅረብ ተብሎ በ28/3/15ዓ.ም በመታዘዙ ለተጠሪዎች ጥሪ ተደርጎ 1ኛ እና 2ኛ ተጠሪዎች በ30/5/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት መልስ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ነው የሚሉበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲሻር፤ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ሕዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት እና የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የሰጡት ውሳኔ እንዲጸና፤ ወጪና ኪሳራ እንዲከፈላቸው እንዲወሰንላቸው ጠይቀዋል፡፡ 3ኛ ተጠሪ በ30/5/15ዓ.ም በተጻፈ ባቀረበው መልስ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ ሆነ የህግ ስህተት አልተፈጸመበትም የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር እንዲጸና ጠይቋል፡፡ አመልካቾች ተጠሪዎች ባቀረቡት መልስ ላይ የመልስ መልስ አቅርበዋል፡፡

ይህ የሰበር ሰሚ ችሎትም የአመልካቾችን የሰበር አቤቱታ አቤቱታ ከቀረበበት ውሳኔ እና ከተገቢዎቹ የህግ ድንጋጌዎች አንጻር የስር ፍ/ቤቶች ውሳኔ መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት መሆን አለመሆኑን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በሰ.መ.ቁ 52041(ቅጽ 10) የስረ-ነገር ስልጣን በህግ ባልተሰጠው የዳኝነት አካል(ፍርድቤት) የተሰጠ ፍርድ የማይጸና ስለመሆኑ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቷል፡፡ የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 154/2013 አንቀጽ 25(2) የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ዋጋቸው በገንዘብ የማይገመቱ ፍታብሔር ነክ ጉዳዩችን የማየት የዳኝነት ስልጣን ያለው መሆኑን ደንግጓል፡፡ ይህ አዋጅ በክልሉ ምክር ቤት ከጸደቀበት ነሀሴ 17 ቀን 2013ዓ.ም ጀምሮ የጸና እንደሆነ የአዋጁ አንቀጽ 61 ደንግጓል፡፡ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 59(1) የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች በሚለው አርእስት ስር አዋጁ ስራ ላይ በዋለበት ግዜ በክልሉ ፍ/ቤቶች በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮች በተጀመሩበት መንገድ ፍጻሜ የሚያገኙ መሆኑን ደንግጓል፡፡

የቀድሞው የሐረሪ ህዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 (ከመደበኛ ፍርድቤቶች ስልጣን ውጪ ባሉ ጉዳዮች የሐረሪ ሕዝብ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988ን ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥሮች 17/1991፤ 68/1999፤ 107/2004 መሻሻሉ እንደተጠበቀ ሆኖ) አንቀጽ 17(1) የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት በክልሉ ስልጣን ስር ባሉ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርአት፤ የፍታበሄር ስነስርአት ህግ እና በሌሎች ሕጎችና ደንቦች ቀድሞ በአውራጃና በወረዳ ፍርድቤቶች እንዲታዩ የተደነገጉትን በመጀመሪያ ደረጃ ተቀበሎ የማየት የዳኝነት ስልጣን ይኖረዋል በማለት ደንግጓል፡፡

በያዝነው ጉዳይ አመልካቾች በስር የሀረሪ ህዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት በተጠሪዎች ላይ በ30/10/12ዓ.ም በተጻፈ ባቀረቡት የፍታብሄር ክስ የጠየቁት ዳኝነት በገንዘብ የማይገመት ስለመሆኑ ከቀረበው ክስ ይዘት የምንገነዘበው ነው፡፡ ክሱም የተጀመረው እና ውሳኔ ያገኘው የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 154/2013 በክልሉ ምክር ቤት በ17/12/13ዓ.ም ከመጽደቁ በፊት እንደመሆኑ ለጉዳዩ ተፈጻሚነት ያለው በሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት ፍርድቤቶችን እንደገና ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 154/2013 አንቀጽ 60(1) ድንጋጌ መሰረት የተሻረው የሀረሪ ህዝብ ክልላዊ መንግስት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍ/ቤቶች እና የዳኞች አስተዳደር ጉባኤን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1988 ነው፡፡ የዚህ አዋጅ አንቀጽ 17(1) ከላይ እንደተዘረዘረው የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ተቀብሎ እንዲያይ ከተሰጡት ስልጣኖች አንዱ በክልሉ ስልጣን ስር ባሉ ጉዳዮች በኢትዮጵያ የፍታብሔር ስነስርአት ህግ ቀድሞ በአውራጃና በወረዳ ፍ/ቤቶች እንዲታዩ የተደነገጉትን ጉዳዮች ነው፡፡

የፍታብሔር ስነስርአት ህግ አንቀጽ 18 በህጉ በቁጥር 15(2) እና (3) የተነገረው ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በገንዘብ ግምት ሊወሰን በማይችል ሀብት ምክንያት የሚቀርብ ክስ የሚታየው ክሱ በተነሳበት አውራጃ ግዛት ፍርድቤት ነው፡፡ ከነዚህ ድንጋጌዎች አንጻር በተያዘው ጉዳይ በአመልካቾች የቀረበውን በገንዘብ የማይገመት ዳኝነት በመጀመሪያ ደረጃ ተቀበሎ የማየት ስልጣኑ የሀረሪ ክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድቤት ነው፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ የሀረሪ ህዝበ ከፍተኛ ፍ/ቤት በአመልካቾች የቀረበውን ክስ ለማየት የስረነገር ስልጣን የሌለው በመሆኑ ክሱ ሲቀርብለት ጉዳዩን ለማየት የስረነገር ስልጣን የለኝም በማለት መዝገቡን ሊዘጋው ሲገባው ክሱን ተቀበሎ ክርክሩን መርቶ የሰጠው ውሳኔ እና ጉዳዩን በይግባኝ እና በሰበር ደረጃ ያዩትም የክልሉ የበላይ ፍ/ቤቶች የስር ፍ/ቤቱን ውሳኔ ሳያርሙ በየራሳቸው የሰጡት ውሳኔ ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት የፌደራል ፍ/ቤቶች አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀጽ 2(4)(ረ) እና(ሸ) እንዲሁም አንቀጽ 10(1)(ሐ) ከደነገጉት አንጻር ሊታረም የሚገባው መሰረታዊ የሆነ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝቶታል፡፡ ስለሆነም ተከታዩ ተወስኗል፡፡

## <u>ውሳኔ</u>

1. የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረሪ ሕዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ.ቁ 20189 በ20/7/13ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 05597 በ11/4/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ እንዲሁም የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ.ቁ 00274 በ21/10/14ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡
2. የሐረሪ ሕዝብ ክልላዊ መንግስት የሐረሪ ሕዝብ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካቾች በተጠሪዎች ላይ ያቀረቡትን ክስ ተቀበሎ የማየት የስረነገር ስልጣን የለውም በማለት ይህ የሰበር ሰሚ ችሎት በፍ/ብ/ስ/ስ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ወስኗል፡፡
3. የዚህ ውሳኔ ግልባጭ ለስር ፍ/ቤቶች ይድረስ፡፡
4. መዝገቡ ውሳኔ ስላገኘ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !